## በአስቸኳይ ጠበቃ ለማነጋገር የምፈልግ ከሆነ የት መሄድ አለብኝ?

ከታች የተጠቀሱት ቦታዎች በአካል በመሄድ ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።.

ምዝገባ፡- 6:00 p.m. – 6:30 p.m. (ያሉት ቦታዎች የተወሰኑ ናቸው)

**ኢስት-ኮውንቲ ኮምዩኒቲ ሪክሬሽን ማዕከል (East County Community Recreation Center)**
3310 Gateshead Manor Way
Silver Spring, MD 20904
ወር በገባ 2ኛው እና 4ኛው ሰኞ ቀን ላይ

**ጌተርስበርግ ቤተ መፃሕፍት [Gaithersburg Library]**
**ጊልክረስት የስደተኞች ሪሶስርስ ማዕከል (Gilchrist Immigrant Resource Center) ፡-**
18330 Montgomery Village Avenue
Gaithersburg, MD 20879
ወር በገባ 1ኛው እና 3ኛው ሐሙስ ቀን ላይ

**ቴስ ኮምዩኒቲ አክሽን ሴንተር [TESS Community Action Center]**
8703 Flower Avenue
Silver Spring, MD 20901
8703 Flower Avenue
ወር በገባ 1ኛው እና 3ኛው እሮብ ቀን ላይ

**ዌስትፊልድ ሳውዝ ሕንፃ ዊተን [Westfield South Building Wheaton]**
**ጊልክረስት የስደተኞች ሪሶስርስ ማዕከል (Gilchrist Immigrant Resource Center)፡-**
11002 Veirs Mill Rd., Suite 506
Wheaton, MD 20902
ወር በገባ 2ኛው እና 4ኛው እሮብ ቀን ላይ

**እባክዎ ያስታውሱ፡**

ደንበኞች መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ ይስተናገዳል በሚል መርህ አይስተናገዱም ነገር ግን በሚፈለገው የህግ ዘርፉ ላይ በተካነ ጠበቃ ይስተናገዳሉ።.

## የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራምን ለማግኘት ብቁ ካልሆንኩኝስ?

የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም ከእርስዎ የህግ ጉዳይ ጋር በተያያዘ እርስዎን ሊያግዙ ከሚችል ወደ ሌላ ኤጀንሲ ወይም ፕሮግራም ሊመራዎት ይችላል። የገቢ መጠንዎ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ብቁ ካልሆኑ ወይም የእርስዎ የህግ ጉዳይ በፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም በኩል ሊስተናገድ የማይችል ከሆነ፣ በሚከተሉት የህግ አገልግሎት አቅራቢዎች በኩል ጠበቃ ለማግኘት ይችላሉ፡-

**የጠበቃ ሪፈራል አገልግሎት**
በሚፈልጉት የህግ ዘርፍ ላይ የተካነ/ነች ጠበቃ ማግኘት እና ጥቆማ መስጠት ላይ ተወካያችን ሊያግዞት ይችላል። የጠበቃ ሪፈራል (ጥቆማ) አገልግሎት በስልክ ቁጥር (301) 279-9100 ላይ ከሰኞ - አርብ ከጠዋቱ 9:00 am - 1:00 pm ድረስ ማግኘት ይችላሉ።.

**የቤተሰብ ህግ የራስ-አገዝ ማዕከል**
ቀላል የቤተሰብ ህግ ክስ መዝገቦች ላይ ያለ ጠበቃ ፍርድ ቤት መቆም ለሚፈልጉ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ከሠራተኞቻችን እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ጠበቆቻችን በኩል የተወሰነ የህግ ማማከር አገልግሎት ወይም አጠቃላይ የህግ መረጃ ማግኘት ይችላሉ። በአካል ቢሮ ለሚመጡ ደንበኞችን በነፃ የሚያስተናግድ የህግ ክሊኒክ ሲሆን የሚገኝበት አድራሻም የሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ ሰርኪዩት ፍርድ ቤት [Circuit Court for Montgomery County, Maryland ] በመንገድ አድራሻ 50 Maryland Avenue, Room 1500 South Tower Rockville, MD 20850 ላይ ነው; የስራ ቀን እና ሰዓት ሰኞ፣ እሮብ፣ ማክሰኞ እና አርብ ከጠዋቱ 8:00 am እስከ ቀትር በኋላ 4:30 pm ድረስ ነው እና ማክሰኞ ደግሞ ከጠዋቱ 8:00 am እስከ ምሽቱ 8:00 pm ድረስ ነው።.

ባር ፋውንዴሽን ኦፍ ሞንጎመሪ ካውንቲ [Bar Foundation of Montgomery County] የ 501 (c) (3) ድርጅት ሲሆን፣ ለድርጅቱ የሚሰጡ መዋጮዎች ከታክስ ተቀናሽ ናቸው። የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም አገልግሎቶች የሚደጎሙት በሜሪላንድ ሌጋል ሰርቪስስ ኮርፖሬሽን [Maryland Legal Services Corporation] እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ [Montgomery County Department of Health and Human Services] በኩል ነው።.

ኖቬምበር 2023

BAR FOUNDATION
OF MONTGOMERY COUNTY

# የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም

ጠበቃ የሚፈልጉ ከሆነ ነገር ግን ለመቅጠር አቅም የሌሎት ከሆነ ...

በፕሮ ቦኖ ነፃ የሕግ ማማከር ፕሮግራም በኩል ከፈቃደኛ የህግ ጠበቃዎች ነፃ እገዛ ማግኘት ሊችሉ ይችላሉ



## የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎት ምንድን ነው?

የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎት የፍትሃብሔር ጉዳዮች ላይ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የካውንቲው ነዋሪዎች ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎት ይሰጣል። የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም ለነዋሪዎቹ ነፃ አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሁለት አማራጮችን ይሰጣል - እነዚህም የህግ ማማከር አገልግሎት መስጫ ኪሊኒክ ውስጥ የሚሰጥ ወይም በቀጥታ የጥብቅና አገልግሎት ለማግኘት የበጎፈቃድ ጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ከሆነ ጠበቃ ጋር እንዲገናኙ የሚያስችል የደንበኛ መቀበያ ስልክ መስመር በኩል ናቸው።.

ማን ነው ብቁ የሚሆነው?

ደንበኞች ብቁ ለመሆን የሚከተሉት መስፈርቶችን በሙሉ ማሟላት አለባቸውe:

- ·የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ መሆን አለብዎ
- የሜሪላንድ የገቢ እርከን ብቁነት መመሪያዎችን ማሟላት አለብዎት
- በፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም ውስጥ የሚሰሩት የበጎፈቃድ ጠበቃዎች ልይዙት የሚችሉትን የህግ ዘርፍ ላይ ድጋፍ ለማግኘት መጠየቅ አለብዎ



## በፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም በኩል የሚስተናገዱ የክስ አይነቶች

- የጋብቻ ፍቺ ማጽደቅ
- የፍቺ ስምምነቶች
- የልጅ አሳዳጊነት መብት ሁኔታ
- የጉዲፈቻ/የሞግዚትነት
- ቀላል የስም ለውጦች
- የኪሳራ ማወጀ (ቀላል ምዕራፍ 7)
- የተወሰነ ዕዳ መሰብሰብ ሁኔታ
- የግል አከራይ ተከራይ (የቤት ክራይ የመጠባበቂያ ተቀማጭ ገንዘብ ብቻ)
- የተወሰኑ የኢሚግሬሽን የክስ መዝገቦች (ቀላል የአቋም ደረጃ ለውጦች)
- የውርስ ኑዛዜዎች እና ውክልናዎች

## በፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም በኩል የማይስተናገዱ የክስ አይነቶች

(ሌጋል ክሊኒክ ውስጥ እነዚህን አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ)

- ·የድንገተኛ ጊዜ ክስ መዝገቦች
- ·የወንጀል እና የትራፊክ ክስ መዝገቦች
- ·የማህበራዊ ደህንነት፣ ስራ አጥነት ወይም የሰራተኞች ካሳ ክስ መዝገቦች
- ·ማንኛውም ክፍያ-የሚያስከትሉ ክስ መዝገቦች
- ·የሕዝብ ጥቅማጥቅሞች
- ·የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች ጉዳይ
- ·የቀለብ/የልጅ ማሳደጊያ ተቆራጭ ገንዘብ/የልጅ ጉብኝት ሰዓት (የልጅ አሳዳጊነት መብት/የፍቺ ክስ ሂደት አካል ያልነበሩ ከሆነ)
- ·የይግባኝ ጥያቄዎች
- የድህረ-ፍርድ ቤት ማዘዣ አቤቱታዎች (የፍርድ ቤት ማዘዣዎች፣ ማስከበሮች፣ ወይም ማንኛውም የሚቀየሩ የክስ ሂደቶች)

The Pro Bono Program is committed to helping the residents of Montgomery County, MD. Individual circumstances may vary and in some cases we may not be able to assist everyone.

## በነፃ ጠበቃ ለእኔ እንዲቆምልኝ ለማድረግ ምን ማድረግ አለብኝ?



የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር አገልግሎትን ለማግኘት እዚህ ላይ ይደውሉ፦

(301) 424-7651

9:00 am - 3:00 pm

ከሰኞ - ሐሙስ

እና የመጀመሪያ የብቁነት ማጣሪያ ጥያቄዎችን ይለፉ።

(እባክዎ ያስታውስ በአካል ቢሮ በመምጣት የማጣሪያውን ሂደት መፈጸም አይችሉም)

- በመጀመሪያው የማጣሪያ መስፈርት መሰረት፣ ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም ለእኛ በአስር የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ተሞልተው መላክ ያለባቸውን ቅጾች ይልክሎታል። እርስዎ ከሞሉት ማመልከቻ ጋር ተመላሽ የማይደረግ የ **$25.00** ዶላር የስራ ማስፈጸሚያ ክፍያ (በካሸርስ ቼክ [Cashier's Check] ወይም በመኒ ኦርደር [Money Order] ብቻ) አያይዘው መላክ አለብዎት።.
- ብቁ እንደሆኑ ከተወሰነ በኋላ፣ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃዎች ሞልተው ከላኩ በኋላ፣ የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም ጠበቃ እንዲያገኙ በተጠባባቂ ዝርዝር ውስጥ ያስቀምጦታል። የበጎ ፈቃደኞች ጠበቃ የእርስዎ ክስ ጉዳይ ለማየት እና ጥብቅና ለመቆም ሲስማማ፣ የጠበቃው ስም እና ስልክ ቁጥር የያዘ ደብዳቤ ይላክሎታል። ሁሉንም ቀጠሮዎች ለማስያዝ ጠበቃዎን መከታተል እና ማግኘት አለብዎ።.
- የእርስዎን ክስ መዝገብ ጠበቃ እንዲይዘው ለማድረግ ማንኛውም ጥረት ይደረጋል፣ ሆኖም ግን፣ ጠበቃ እንደምናቀርብሎት እርግጠኛ ማስተማመኛ መስጠት አንችልም።.

## በአስቸኳይ ጥብቅና ሊቆምልኝ የሚችል ጠበቃ ማግኘት እችላለሁ?

**አይ።** የፕሮ ቦኖ ነፃ የህግ ማማከር ፕሮግራም በበጎፈቃደኞች ላይ የሚመሰረት ነው፣ ስለዚህ እርስዎን ለመወከል የሚችል ጠበቃን ለማግኘት ብዙ ሳምንታትን ሊወስድ ይችላል። በዚህም ምክንያት፣ **ፕሮግራሙ አስቸኳይ የክስ ሁኔታዎች ያላቸውን ሰዎች ማገዝ አይችልም።**